- እግዚአብሔር ፈሪሳዊውን ያልተቀበለው ለምን ነበር?

- ፈሪሳዊው ንጹህ ያልሆነ ልብ እንዳለው ስላላመነ።

- ፈሪሳዊው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላላመነ።

- እግዚአብሔር ቀረጥ ሰብሳቢውን ተቀብሎታል?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ቀረጥ ሰብሳቢውን የተቀበለው ለምን ነበር?

- ቀረጥ ሰብሳቢው ንጹህ ያልሆነ ልብ እንዳለው ስላወቀ።

- ቀረጥ ሰብሳቢው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላወቀ።

- ቀረጥ ሰብሳቢው፥ እንዲያድነው የእግዚአብሔርን ስም ስለጠራ።

- በምሳሌው ማብቂያ ላይ ኢየሱስ ምን አለ?

- ኢየሱስ “በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ የሚያደርገውን እግዚአብሔር ከፍ ያደርገዋል” አለ።

- ኢየሱስ “በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ከፍ የሚያደርገውን እግዚአብሔር ዝቅ ያደርገዋል” አለ።



## ትምህርት 58

1. ብዙ ሕዝብ ኢየሱስን የተከተለው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ሕዝቡ ኢየሱስ በበሽተኞች ላይ የሚያደርጋቸውን ተአምራዊ ምልክቶች ለማየት ስለፈለጉ ነው።

2. ኢየሱስ ሕዝቡን መመገብ ሲጀምር ስንት እንጀራና ስንት ዓሣ ነበሩት?

ሀ- አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ።

3. በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ኢየሱስ ስንት ሰዎችን መገበ?

ሀ- ከአምስት ሺህ ሕዝብ በላይ።

4. ኢየሱስ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ከአምስት ሺህ ሕዝብ በላይ እንዴት ሊመግብ ቻለ?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ።

ለ- ምክንያቱም ኢየሱስ ማናቸውንም ነገር ማድረግ ስለሚችል።

5. ሕዝቡ ኢየሱስን ለማንገሥ የፈለጉት ለምን ነበረ?

ሀ- ኢየሱስ ሁልጊዜ እንጀራ እንዲሰጣቸው ስለ ፈለጉ።

6. ኢየሱስ በሕዝቡ ላይ መንገስ ያልፈለገው ለምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ የሕዝቡ ልብ ክፉ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር።

ለ- ኢየሱስ ሕዝቡ ሊያነግሡት የፈለጉት እንጀራ እንዲሰጣቸው ስለፈለጉ ብቻ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር።

7. ኢየሱስ እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ከሰጣቸው መና ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነበር?

ሀ- መና ከሰማይ እንደ ወረደ ሁሉ ኢየሱስም ከሰማይ በመውረዱ።

ለ- መና የተሰጠው በእግዚአብሔር እንደ ሆነ ሁሉ ኢየሱስም ከእግዚአብሔር የተሰጠ በመሆኑ።

ሐ- እስራኤላውያን መናውን ካልበሉ እንደሚሞቱ ሁሉ ሰዎች በኢየሱስ ካላመኑ የሚሞቱ በመሆናቸው።

- አንድ ቀን ጥቂት ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ኢየሱስን ሊጎበኙት መጡ።

ማርቆስ 7፡1-5

1- ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳንድ ጸሐፍት በዙሪያው ተሰበሰቡ፤

2- ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ ባልነጻ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ፤

3- ፈሪሳውያንና አይሁድ ሁሉ የአባቶችን ወግ ለመጠበቅ ሲሉ፣ በሥርዐቱ መሰረት እጃቸውን በጥንቃቄ ሳይታጠቡ አይበሉም ነበርና።

4- ከገበያ ሲመለሱም ታጥበው ራሳቸውን ካላነጹ በስተቀር አይበሉም ነበር። እንዲሁም ዋንጫን፣ ማሰሮን፣ ሳሕንና ዐልጋን እንደ ማጠብ ያሉትን ሌሎችን ወጎች ይጠብቁ ነበር።

5- ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ «ደቀ መዛሙርትህ እንደ አባቶች ወግ በመኖር ፈንታ ባልታጠበ እጃቸው ለምን እንጀራ ይበላሉ?» ብለው ጠየቁት።

- ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን (ጸሐፍት) በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ላይ የተቆጡት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የአባቶችን ወግ ስላልጠበቁ ነበር።



- ቀረጥ ሰብሳቢው ስለ ራሱ ምን ያስብ ነበር?

- ቀረጥ ሰብሳቢው ልቡ ንጹሕ አለመሆኑን ያውቅ ነበር።

- ቀረጥ ሰብሳቢው ልቡ ንጹሕ ያለመሆኑን እንዴት አወቀ?

- ምክንያቱም ክፉ አሳቦቹ ከልቡ የመነጩ መሆናቸውን ስለተረዳ ነው።

- ቀረጥ ሰብሳቢው ኃጢአተኛ መሆኑንና በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ያውቅ ነበር።

- እርሱ የረከሰውን ልቡን መለወጥ እንደማይችል ያውቅ ነበር።

- ለኃጢአቱ የሚገባው ቅጣት ሞት መሆኑን ያውቅ ነበር።

- ቀረጥ ሰብሳቢው እንዲያድነው የእግዚአብሔርን ስም ጠራ።

- ቀጥሎስ ኢየሱስ ምን አለ?

ሉቃስ 18፡14

14- ኢየሱስ እንዲህ አለ «እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ ይኸኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጻድቅ ተቈጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።»

- እግዚአብሔር ፈሪሳዊውን ተቀበለው?

- አልተቀበለውም።

- ፈሪዊው ስለ ራሱ ምን አሰበ?

- ፈሪሳዊው “ልቤ ንጹሕ ነው” ብሎ አሰበ።

- ፈሪሳዊው “ልቤ ንጹሕ ነው” ብሎ ያሰበው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እርሱ የአባቶችን ወግ ይጠብቅ ስለነበር ነው።
- ምክንያቱም እርሱ በሳምንት ሁለት ቀን ይጾም ስለነበር ነው።

- ምክንያቱም ከሚያገኘው ሁሉ ዐሥራቱን ለቤተ መቅደስ ያወጣ ስለነበር ነው።

- ፈሪሳዊው በጣም ታብዮ ነበር።

- እርሱ “መልካም ሰው ነኝ” ብሎ ያስብ ነበር።

- እርሱ የሠራቸውን ስራዎች ሁሉ መልካም እንደሆኑ አሰበ።
- እርሱ ከሌሎች ሰዎች የተሻለ መሆኑን አሰበ።

- ፈሪሳዊው አዳኝ እንደሚያስፈልገው አላመነም።

- ቀረጥ ሰብሳቢውስ?

ሉቃስ 18፥13

13- [ኢየሱስ እንዲህ አለ] «ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት ቆሞ፣
ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልፈለገም፤ ነገር ግን ደረቱን እየደቃ፣
‘እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ’ ይል ነበር።»



- የአባቶች ወግ ምን ነበር?

- እነዚህ ወጎች ፈሪሳውያኑ ራሳቸው የፈጠሩአቸው ወጎች ሲሆኑ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኝ እነዚህን ወጎች መጠበቅ አለባቸው ይሉአቸው ነበር።

- ከምንጠብቃቸው ወጎች የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላለን?

- አንችልም።

- ፈሪሳውያኑ የፈጠሩአቸውን ወጎች በመጠበቃቸው እግዚአብሔር እንዳጸደቃቸው ያምኑ ነበር።

- ፈሪሳውያኑ ወጎችን ሁሉ ቢጠብቁም ልባቸው ግን ክፉ ነበር።

- ወጎችን መጠበቅ ልባችንን ያነጻል?
- አያነጻም።

- ፈሪሳውያን ውጫዊ ሥርዓቶችን ሁሉ ቢጠብቁም እንኳን ልባቸው ግን በክፋት የተሞላ ነበር።

- ድስታችሁ የዶሮ ኩስ በውስጡ ቢኖርበት የማሰሮውን ወጫዊ ክፍል ማጠብ ውስጡን ለማንጻት ይረዳል?

- አይረዳም።
- ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ምን አላቸው?

ማርቆስ 7፡6

6- እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ኢሳይያስ ስለ እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል ተንብዮአል፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤ ‘ይህ ሕዝቡ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው።’»

- ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ግብዞች አላቸው።

- ግብዝ ምንድን ነው?

- ግብዝ ንግግሩና ተግባሩ የማይስማማና ሙሉ በሙሉ የተለያየ ሰው ነው።

- ኢየሱስ፥ በተጨማሪም ስለ እነርሱ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ላይ በነቢዩ በኢሳይያስ የተጻፈው ነገር እውነት መሆኑን ተናገረ።

- ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ እነዚህ ሰዎች የተናገረው ምን ነበር?

- ነቢዩ ኢሳይያስ “ሕዝቡ በአፉ በእግዚአብሔር እናምናን ይላሉ ልቡ ግን ከእግዚአብሔር የራቀ ነው” አለ።

- ነቢዩ ኢሳይያስ እነርሱ እግዚአብሔርን የሚያምኑት በአፋቸው እንጂ ከልባቸው አይደለም አለ።

- እግዚአብሔር በንግግራቸው ብቻ በእግዚአብሔር እናምናለን የሚሉትን ይቀበላል?

- አይቀበልም።



- እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያለውን ርኩሰት ያያል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ልባችን ሁሉ በክፋት መሞላቱን ያያል።

- በልባችን ውስጥ ያሉት ክፋቶች ምን ምንድን ናቸው?

- ክፉ አሳብ ዝሙት ሌብነት ሰው መግደል ማመንዘር ስግብግብነት ክፋት ማታለል መዳራት ምቀኝነት ስም ማጥፋት ትዕቢት ስንፍና ናቸው።

- ቀጥሎ ኢየሱስ ለሕዝቡ ምሳሌ ተናገረ።

ሉቃስ 18፡9-12

9- ራሳቸውን እንደ ጻድቃን በመቍጠር ለሚመኩና ሌሎቹን በንቀት
ዓይን ለሚመለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤
10- «ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ፣ አንዱ
ፈሪሳዊ፣ ሌላው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር።
11- ፈሪሳዊውም ቆሞ ስለ ራሱ እንዲህ ይጸልይ ነበር፤
«እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ቀማኛ፣ ዐመፀኛ፣
አመንዝራ፣ ይልቁንም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ባለመሆኔ አመሰግንሃለሁ፤
12- በሳምንት ሁለት ጊዜ እጾማለሁ። ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት
አወጣለሁ።»

- ኢየሱስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ ወደ ቤተ መቅደስ ሊጸልዩ የሄዱ ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ?

- አንደኛው ፈሪሳዊ ሲሆን ሌላኛው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር።

ማርቆስ 7፡20-23

20- ኢየሱስ «ቀጥሎም እንዲህ አለ፤ «ከሰው የሚወጣ ያ ሰውን ያረክሰዋል፣

21- ከውስጥ፥ ከሰው ልብ የሚወጡት ምንዝር፥ ስርቆት፣ ሰው መግለድ፣ ዝሙት፣

22- መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው።

23- እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ። ሰውንም ያረክሱታል።»

- ኢየሱስ ሰውን የሚያረክሰው ምንድን ነው አለ?
- ሰውን የሚያረክሰው ከውስጥ የሚወጣ ነገር ነው አለ።

- ከውስጥ ሆኖ ሰውን የሚያረክሰው ምንድን ነው?
- ልቡ ነው።

- አዳምና ሔዋን በዔድን የአትክልት ስፍራ ኃጢአት በመሥራታቸው ልባቸው ረከሰ።

- ቃየንና አቤል በረከሰ ልብ ተወለዱ።

- አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ሁሉም በረከሰ ልብ ተወለዱ።

- እስራኤላውያን ሁሉ በረከሰ ልብ ተወለዱ።
- ሰዎች ሁሉ በረከሰ ልብ ተወለዱ።

- ሰዎች ሁሉ በረከሰ ልብ ስለ ተወለዱ ርኩሰት የሚወጣው ከልባችን ነው።



- ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ሌላ ምን አላቸው?

ማርቆስ 7፡7-9

7- ኢየሱስ እንዲህ አለ «በከንቱ ያመልኩኛል፤ ትምህርታቸውም ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው።

8- የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ የሰዎችን ወግና ሥርዐት ትጠብቃላችሁ።»

9- ደግሞም፣ እንዲህ አላቸው፤ «የራሳችሁን ወግ ለመጠበቅ ስትሉ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የምትተውበት ዘዴ አላችሁ።»

- ኢየሱስ ፈሪሳውያን እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በከንቱ መሆኑን ተናገረ።

- ፈሪሳውያን እግዚአብሔርን በከንቱ ያመለኩት እንዴት ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የእነርሱን አምልኮ ስለማይቀበል።

- እግዚአብሔር የፈሪሳውያንን አምልኮ ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም የእነርሱ አምልኮ ከአፋቸው ብቻ እንጂ ከልባቸው ስላልሆነ ነበር።

- ምክንያቱም የእነርሱ አምልኮ ከሥጋቸው እንጂ ከልባቸው ስላልሆነ ነበር።

- ፈሪሳውያን ወጋቸውን በመጠበቃቸው ምን እያደረጉ ነበር?
- የእግዚአብሔርን ትእዛዞች እያፈረሱ ነበር።

- እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሳቸውን ወጎች እንዲጨምሩ ይፈልጋል?

- አይፈልግም።

- እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት በተናገረው ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ የለብንም።

- ኢየሱስ ለፈሪሳውያኑ ይህን ከተናገረ በኋላ ሕዝቡን ወደ ራሱ ጠራ።

ማርቆስ 7፥14-15 እና 17-19

14- ደግሞም ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «ስሙኝ፤ ሁላችሁም አስተውሉ፤

15- ከውጭ ወደ ውስጥ ገብቶ ሰውን የሚያረክሰው አንዳች ነገር የለም፤ ይልቁን ሰውን የሚያረክሰው ከራሱ ወደ ውጭ የሚወጣው ነገር ነው።»

17- ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት።

18- እርሱም፣ «እናንተም ነገሩ አይገባችሁምን? ከውጭ ወደ ሰው ገብቶ ሊያረክሰው የሚችል አንዳች ነገር የለም፤

19- ወደ ልቡ ሳይሆን ወደ ሆዱ ይገባል፤ ከዚያም ከሰውነቱ ይወጣልና።» ኢየሱስ ይህን በማለቱ ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን ገለጠ።

- ኢየሱስ ለሕዝቡ ምን አለ?
- ኢየሱስ “ከውጭ ወደ ውስጥ ገብቶ ሰውን የሚያረክሰው ነገር የለም” አለ።

- ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?



- ኢየሱስ “ሰዎች ባልታጠበ እጅ ወይም በርኩስ ምግብ ምክንያት ሊረክሱ አይችሉም” ማለቱ ነበር።

- ሰዎች ባልታጠቡ እጆች ወይም በረከሰ ምግብ ምክንያት የማይረክሱት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ያልታጠበ እጅና የረከሰ ምግብ ልብን መንካት ስለማይችሉ ነው።

- ኢየሱስ “የእጅ እድፍና የረከሰ ምግብ ወደ ሆድ ይገባሉ ከዚያም ከሰውነታችን ይወጣሉ እንጂ ልባችንን አይነኩም” አለ።

- በበላነው ምግብ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?
- አናገኝም።

- ሳንበላ በተውነው ምግብ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?
- አናገኝም።

- የምንለብሰው ልብስ ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?
- አናገኛኝም?

- ሳንለብሳቸው በተውናቸው ልብሶች ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እናገኛለን?

- አናገኝም።
- ኢየሱስ ሌላ ምን አለ?